**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ/መ/ቁ 239802

ጥቅምት 1 ቀን 2016 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንደሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች ፡-** ረ/ሳጅን ሰብለ በትሩ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች ፡-** 1ኛ. ወ/ሮ አበበች ደመሴ
2ኛ. አቶ ታደሰ በትሩ
3ኛ. ወ/ሮ አጸደ በትሩ
4ኛ. አቶ በለጠ በትሩ
5ኛ. አቶ ደቻሳ በትሩ
6ኛ. አቶ ግሩም በትሩ
7ኛ. አቶ ክንፈ በትሩ
8ኛ. ወ/ሮ ሰላማዊት በትሩ

} ጠበቃ በብርሃኑ በቀለ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# **ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክርክርን የተመለከተ ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ክርክሩ በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጀመረው የአሁን አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከ2-8 ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች ወደ ጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሰኔ 29 ቀን 2013 ዓ/ም ለስር ፍርድ ቤት ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባቴ አቶ በትሩ ሊባኖሴ ከዚህ ዓለም በቀን 16/3/2011 ዓ/ም በሞት ተለይቷል፤ ሟች አባቴ በሕይወት በነበረበት ጊዜ የተለያዩ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ (በክሱ የዘረዘሩ) ንብረቶች አፍርቷል፡፡ ነገር ግን ተከሳሽ (የአሁን 1ኛ ተጠሪ) ከዚህ ንብረት የውርስ ድርሻዬን ለማካፈል ፈቃደኛ ስላልሆነች አጠቃላይ ድርሻዬን ብር 2,387,500.00 የሚያወጣ ንብረት ልታካፍል ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ ባቀረቡት መቃወሚያ ሟች በህይወት እያሉ በቀን 12/8/2010 ዓ/ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ ከሳሽን ጨምሮ ወራሾች ለሆኑ 8 (ስምንት) ልጆች ድርሻቸውን ተናዝው ኑዛዜው በኩዩ ወረዳ ፍ/ቤት በ/መ/ቁ 51513 ጸድቆ በኑዛዜው መሰረት ክፍፍል ተደርጓል፡፡ አመልካች በኑዛዜው መሰረት ድርሻዋ እንዲሰጣት በሀገር ሽማግሌ ጠይቃ በ04/11/2011 ዓ.ም ብር 50000.00 (ሀምሳ ሺህ) በባንክ ሂሳቧ ገቢ የተደረገላት ሲሆን የገጠር መሬት ይዞታ ዱበና አገሎ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ የተናዘዘላትን 2700 ካ.ሜ ወስዳለች፡፡ አሁን እንዳልወሰደች በማስመለሰል ክስ ያቀረበችው አላግባብ በመሆኑ አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244 (2) እና 245 (1) መሰረት ውድቅ እንዲደረግ፤ እንዲሁም ክርክር ባስነሳው ንብረት መብት የሌላት በመሆኑና ንብረቱን ሌሎች ወራሾች በኑዛዜው መሰረት በእጃቸው ያስገቡ በመሆኑ ከ2-8 የተዘረዘሩት የአሁን ተጠሪዎች ጣልቃ እንዲገቡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ይስጥልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከተራ ቁጥር 2-8 የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጣልቃ እንዲገቡ ተደርጎ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የመቃወሚያ ክርክሩን መርምሮ ሟች በቀን 12/08/2010 ዓ/ም በተውት ኑዛዜ መሰረት የኑዛዜ ድርሻዋን ብር 50000.00 (ሀምሳ ሺህ) እና የገጠር መሬት የወሰደች በመሆኑ ክሱን ለማቅረብ መብት የላትም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33 (2) እና የፍ/ብ/ህ/ቁ 973/3/ ን ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ እና ሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ ኑዛዜውን በተመለከተ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በስር ፍ/ቤት በንብረት ዝርዝር ተራቁጥር 4.7 ላይ የተጠቀሰው ታርጋ ቁጥር ኦሮ 3-33524 ሃይሩፍ መኪና ፤ በተራቁጥር 4.5 ላይ የተጠቀሰው ይዞታ እና መኖሪያ ቤት እንዲሁም በተራ ቁጥር 1.6 ላይ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤት ሟች በተውት ኑዛዜ ውስጥ ያልተካተቱና አመልካች እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ክፍፍል እንዲደረግ ጥያቄ አቅርቤ እያለ የስር ፍ/ቤት ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ውሳኔው እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት አመልካች ድርሻዋን ወስዳለች በማለት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ሲደረግ በኑዛዜው ላይ ያልተካተቱ የውርስ ንብረቶች መኖር አለመኖሩ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት አቅርባ የነበረው ማመልከቻ የሟች አባቴ አቶ በትሩ ሊባኖሴ የውርስ ድርሻ ይዞታና ንብረት ላይ ላገኝ የሚገባው ድርሻዬ ስላልተካፈለ እንድካፈል ይወሰንልኝ በሚል ነው፡፡ እኛ ተጠሪዎችም የአባታችን ኑዛዜ ተነቦላት ድርሻዋን የወሰደች ስለሆነ ክሷ ተቀባይነት እንዳያገኝ ተከራክረን የስር ፍ/ቤትም ክሷን ውድቅ አድርጓል፡፡ የስር ፍ/ቤት ክሷን ውድቅ ያደረገው ለአመልካች የውርስ ድርሻ በጥያቄዋ መሰረት ተሰጥቷታል ወይስ አልተሰጣትም? ኑዛዜውን ታውቃላች ወይስ አታውቅም? የሚሉትንና ተያያዥ ጭብጦች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህጎችና ማስረጃውን መርምሮ ሲሆን የውርስ ድርሻ ንብረት ለመካፈል ሽማግሌዎችን ልካ እነዚህም ሽማግሌዎች በጥያቄዋ መሰረት የተደረገው ኑዛዜ ተነቦ እና በጥያቄዋ መሰረት በኑዛዜ ተሰጥቷት የነበረውን ንብረት ፊርማ የወሰደች መሆኑን ፤ በምትወስድበትም ጊዜ በኑዛዜው ላይ ምንም አይነት ተቃውሞ ያላነሳች መሆኑን በተመሳሳይ ቃል መስክረው ነው፡፡ በስር ያላነሳችውን ከኑዛዜ ጋር የተያያዘ ክርክር በዚህ ፍርድ ቤት ልታቀርብ አይገባም፡፡ የመኖሪያ ቤት፣ ቦታ እና የሰሌዳ ቁጥሩ ኦሮ 3-33524 የሆነው ተሽከርካሪ ከኑዛዜ ውጪ ያለ ንብረት ሳይሆን በኑዛዜው ላይ ተጠቅሶ በ1ኛ ተጠሪ እጅ እንዲቀመጥ ኑዛዜ የተደረገበት ነው፡፡ ተሽከርካሪው ሟች በሕይወት ሳለ የጀመረውን ቤት ለመገንባት በ800,000.00 (በስምንት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መቶ ሺ.ህ) ተሸጧል፤ ይህ ንብረት የለም፡፡ በአጠቃላይ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማያያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካሳለፈው ብይን እንዲሁም ከግራቀኙ ክርክር መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ስለ ኑዛዜው ሳያመለክቱ ሟች አባታቸው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ያፈሯቸው የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በ1ኛ ተጠሪ ዕጅ እንደሚገኙና 1ኛ ተጠሪ የውርስ ድርሻ ለማካፈል ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል በአጠቃላይ ድርሻየ ያሉትን ብር 2,387,500.00 የሚያወጣ ንብረት ለመካፈል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ይሁንና ሟች በቀን 12/08/2010 ዓ/ም በተውት ኑዛዜ መሰረት አመልካች የኑዛዜ ድርሻቸውን ብር 50000.00 (ሀምሳ ሺ.ህ) እና የገጠር መሬት መውሰዳቸው ተረጋግጧል፡፡ ኑዛዜውን በተመለከተም በስር ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ አሁን የሚያነሷቸውን ክርክሮች በማንሳት ከኑዛዜው አንጻር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ኑዛዜ እንዳልነበርና በኑዛዜው መሰረት የወሰዱት ድርሻ ስለመኖሩ ሳይገልጹ ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ኑዛዜውን አስመልክቶ አሁን የሚያቀርቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለውም የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካራዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት አይችልም፡፡

ይልቁንም በአጣሪ ችሎቱ ጭብጥ እንደተመለከተው በኑዛዜው ላይ ያልተካተቱ የውርስ ንብረቶች መኖር/አለመኖራቸው ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡

አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር የሰሌዳ ቁጥር ኦሮ 3-33524 የሆነ ሃይሩፍ መኪና ፤ ይዞታ እና መኖሪያ ቤት ሟች በተውት ኑዛዜ ውስጥ ያልተካተቱና ክፍፍል ሊደረግባቸው የሚገቡ ንብረቶች ስለመሆናቸው የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎችም ንብረቶቹን በተመለከተ የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የኑዛዜ ድርሻዋን የወሰደች በመሆኑ ክሱን ለማቅረብ መብት የላትም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33 (2) ጠቅሶ ክሱን በሙሉ ውድቅ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማድረግ ብይን ከመስጠቱ በቀር በኑዛዜው ያልተካተቱ የውርስ ንብረቶችን አስመልክቶ በቀረበው ክርክር ላይ የሰጠው ውሳኔ የለም፡፡

እንደሚታወቀው በሟች መሞት ምክንያት በውርሱ ውስጥ የሚገኙት የሟች መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾቹና ለኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 826(2) እና ተከታይ ድንጋጌዎች ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የሟች ንብረት በውርስ የሚተላለፈው በኑዛዜ እንዲሁም ያለኑዛዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ከህጉ ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው በህጉ አግባብ በኑዛዜ ያልተላለፈ ንብረት ያለኑዛዜ ወራሽ ለሆኑት የማይተላለፍበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

በተያዘውም ጉዳይ አመልካች በኑዛዜው መሰረት ድርሻቸውን ወስደዋል ቢባል እንኳ በኑዛዜው ያልተካተቱ የውርስ ንብረቶች ካሉ ለመጠየቅ መብት የላቸውም አይባልም፡፡ ከመነሻውም ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የቀረቡ በመሆኑ የውርስ ንብረት ነው ያሉትን ለመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ አቤቱታ አቅራቢ ወገን አንደ ክርክሩ በማስረጃ አስደግፎ ቢያስረዳ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ለማመልከት በሚያስችል ደረጃ አቤቱታውን አዘጋጅቶ ካቀረበ፤ እንዲሁም አቤቱታውና ክርክሩ መብቱ ይገባኛል የሚልበትን ምክንያት ሚዘረዝርና የመብቱን ሁኔታ የሚገልፅ ከሆነ ዳኝነቱን ለመጠየቅ መብት የለውም ሊባል እንደማይገባ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች በሽማግሌ ጠይቀው የኑዛዜ ድርሻቸውን ወስደዋል መባሉ ኑዛዜ አላረፈባቸውም የተባሉ ንብረቶችን ለመጠየቅ መብት የላቸውም አያሰኝም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በኑዛዜው መሰረት ወስደዋል የተባለው ድርሻ ኑዛዜ አልተደረገበትም ከተባለው የውርስ ንብረት ተለይቶ አመልካች ከኑዛዜው ውጪ ባሉት ንብረቶች የሚያገኙት ድርሻ ተጣርቶ መኖሩ ከተረጋገጠ የውርስ ድርሻቸውን ያለኑዛዜ እንዲያገኙ አለመደረጉ የሚነቀፍ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሰ/ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 73942 በቀን 22/06/2014 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 397509 በቀን 30/10/2014 ዓ.ም እና የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁ 405348 በቀን 01/02/2015 ዓ.ም ያሳለፉት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. አመልካች የኑዛዜ ድርሻቸውን ወስደዋል በመባሉ ኑዛዜ አላረፈባቸውም የተባሉ ንብረቶችን ለመጠየቅ መብት የላቸውም የሚባልበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ በዚህ ረገድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3. የሰ/ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የተዘጋውን የመዝገብ በማንቀሳቀስ በክሱ ከተመለከቱት ንብረቶች መካከል ኑዛዜ አላረፈባቸውም የተባሉትን ንብረቶች ተለይቶ እንዲቀርብ በማድረግ በአግባቡ በማጣራት ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡

4. በኑዛዜው መሰረት የተደረገውን ክፍፍል አስመልክቶ የተሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡

5. እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

6. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !